

# Tezazu G. Abera

April 20, 1958 - September 15, 2018

የመምርት ትዛዙ የህይወት ታሪክ
መምህርት ትዛዙ አበራ ከአባታቸው ከቀኝ አዝማች ገ/እግዚያብኤር አበራ እና ከእናታቸው ወ/ሮ አብረህት ቢተው በአድዋ ከተማ ሚያዝያ 1951ዓ/ም ተወለዱ.
እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በንግሥተ ሳባ ት/ቤት የ1ኛ እና የ2ኛ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ. በ1971 ዓ/ም በባሌ ክፍለ ሀገር በመምህርነት ሞያ ሰለጠኑ.
በተማሩበት የመምህርነት ሞያ በአምቦ ከተማ እያገለገሉ ሳለ ከባለቤታቸው ከአቶ ወልዱ አርአያ ጋር ተዋዉቀው በ1976 ዓ/ም ትዳር የመሰረቱ ሲሆን የ 6 ልጆችም እናት ነበሩ. ልጆቹም ዳንኤል,ናታን,ምህረት,ሮቤል,ይትባረክ እና ትብለፅ ይባላሉ.

በ 1983 ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተዘዋውረው በዛው በመምህርነት ሞያ ሲያገለግሉ ቆይተው በ1992 ዓ/ም ወደ አሜሪካ ፍሎሪዳ ከተማ ከመላው ቤተሰባቸው ጋር አብረው የመጡ ሲሆን በዚህም ከተማ በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው በማገልገል ላይ ሳሉ በደረሰባቸው የጤና እክል ምክንያት በተለያዩ ሆስፒታሎች ሲረዱ ቆይተው መስከረም 5,2011 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል.